## ክፍል ሁለት

ከፍተኛ ስድስት አያሌ የህዝቡ ልጆች ስቃይ የተቀበሉበትና የተሰዉበት ስፍራ ነው። ስማቸውን ከማስታውሳቸው ጥቂቶቹ ወንድማማቾቹ ያሬድና ፋሲል ላቀው፣ አዛለች፣ፀጋዬ ወልዴና የከፍተኛ 6 ቀበሌ 10 ሊቀመንበር የነበረውና በአንጀኞች ጥቆማ የተያዘው ታጀበ ከሌሎች ስማቸውን ከማላስታውሰው ጋር ጥቅምት/ህዳር 70 ኣ/ም ተገድለው ሬሳቸው ስባተኛ መስቀለኛው መንገድ ላይ ተጥሎዋል። ተፈሪ ፣ከንፈ ደምሴ፣ጌታቸው ከበደ፣ከወላይታ አካባቢ ተይዞ የመጣ ሌላ ወጣት ባንድ ምሽት ተገድለው ሬሳቸው በየቤታቸው በራፈ ላይ ተጥሎዋል። ግድያውን ያካሄዱት ዛሬም በህይወት ያሉት የቀይ ሽብር ኮሚቴው አባላትና አንጃዎች ናቸው። የዚህ ማስታወሻም መሰረታዊ ምክንያት የሆነው ወጣት ተሻለ ተስፋዬም በየካቲት 1970 ከቤቱ በራፍ ላይ በአንጃዎች ጥቆማ ተይዞ የመጣውና ከብዙ ስቃይ በኋላ ላይ ከተጠቀሱት ጓዶቹ ጋር የተገደለው እዚሁ ከፍተኛ ውስጥ ነው። ሞት አይፈሬዎቹ እነ ዕንቁ ደበበ፣ ዮሴፍ በሪ፣ ፍሥሐ እርጎሻ፣ ፈለቀ አለሙ፣ ዘርዬ፣ጎሳዬ ደበላ፣ሐረገወይን አበበ (አዲስ አበባ ከ5ቀ15 ከሌሎች ጓዶቿ ጋር በተጠለሉበት ቤት ውስጥ በታንክ ተከበው እጃችንን ለፋሺስቶች አንሰጥም በማለት ተታኩሰው ከወደቁት ጋር የተሰዋች) ፣ ከፍተኛ 7 ኮልፌ አካባቢ በድርጅት ሥራ ላይ ተይዛ ከሌሎች ጓዶቿ ጋር የተገደለችው የአስራ አምስት አመቷ ወጣት ደብረወርቅ አረጋ ሌሎችም አዕላፋት ከፋሺስቱ መንግስት ታንክ፣ ቢ -አርና ማዴቦዎች ጋር ባደባባይ ተፋልመው መሰዋታቸው ተደጋግሞ መወሳት ያለበት ታላቅ የአርበኝነት ገድል ነው ትውልድ መውረስ ያለበት አኩሪ ቅርስም።

የዚህ አጭር መልእክት ርዕሰ ጉዳይ የሆነው *የክቡር ህሊናና ፅናት* መገለጫ ከሆኑት ሁለት ወጣቶች አንዱ ተሻለ ተስፋዬ ሲሆን በአንጀኞች ጥቆማ ከመኖሪያ ቤቱ በራፍ ላይ ተይዞ ለእስርና ሰቆቃ በመጨረሻም ለመስዋእትነት ወደተዳረገበት ከፍተኛ ስድስት ከመታሰሩ ጥቂት ቀደም ብሎ መርካቶ ከሚገኘው የንግድ ድርጅቱ ውስጥ በህይወት ሳገኘው አይኔን ማመን አልቻልኩም ምክንያቱም በከፍተኛ ደረጃ እየተፈለገ እንደሆነ ስለምገምት ምናልባት ተገድሏል ቢያንስ ደግሞ ታስሯል ብዬ አምን ስለነበረ ነው። እንደወትሮው ሁሉ ለጥቂት ደቂቃዎች ስለወቅታዊ ጉዳዮች ከተነጋገርን በኋላ ለጊዜውም ቢሆን መውጣት ያስብ እንደሆነ በተዘዋዋሪ ስጠይቀው የህዝቡ ልጆች አስከሬን እንደውሻ በየመንገዱ እየተወረወረ እኔ ነፍሴን ለማዳን አልሸሽም ይልቁንም የተመቱና የተበጣጠሱ መዋቅሮችን በተቻለ ፍጥነት ቀጣጥሎ ትግሉን ማጠናከር ነው የሚገባው የሚል ነበር መልሱ። ወቅቱ ከተሞች አካባቢ የነበረው የፓርቲው በተለይም የሊጉ መዋቅር የተመታበትና አብዛኛዎቹ መሪዎቹ የተሰዉበት የተረፉትም የታሰሩበት ትርጉም ያለው ድርጅታዊ ሥራ ማከናወን የማይቻልበት ሁኔታ ላይ የተደረሰበት ጊዜ ነበር።

ተሻለ የወቅቱ ትግል በጠየቀው መሰረት ትምህርቱን ከማቋረጡ በፊት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኤኮኖሚክስ ዲፓርትመንት ተማሪ የነበረ ሲሆን በብሩህ አእምሮው የሚደነቅና ብዙዎች የሚኮሩበት ወጣት ነበር። ተሻለ ከመገደሉ በፊት ይህ ነው የማይባል ተከታታይ ሰቆቃ ተፈጽሞበታል። እናቱም እሱን ስለወለዱ ብቻ ከተያዘበት ማግስት ጀምሮ ታስረው የአንድ ልጃቸውን በደም የተነከረና የተዘለዘለ አካል እያዩ በሀዘን እንዲሰቃዩ የተደረጉ ሲሆን በዚሁ ሀዘን በደረሰባቸው የጤና መታወክ ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል። በተለይም ህመማቸውን አባብሶ ለህልፈት የዳረጋቸው አንድ ጧት ከቤታቸው ሲወጡ ተገድሎ በራቸው ላይ የተጣለውን የልጃቸውን የተሻለን አስከሬን ማየታቸው ነበር። አባቱም ቱጃር ነጋዴ መሆናቸው ሳያንስ የሱ ወላጅ መሆናቸው ተደራራቢ 'ወንጀል' ሆኖ ልጅህን ካላመጣህ በሚል እየታደኑ ነበርና ቤትና ስራቸውን በሙተው ነፍሳቸውን ለማዳን ወደ ትውልድ መንደራቸው (ጉራጌ ገጠር) መሰወርም ተገደው ነበር። ተሻለ ከአባቱ በስጦታ የተበረከተለትን የንግድ ድርጅት ህይወቱን ሳይቀር ለሰጠለት ድርጅትና ለቆመለት ዓላማ ማራመጃ ሙሉ በሙሉ ተጠቅሞበታል።

ተሻለ ውጫዊ ገጽታውን ላየ ለምንም ነገር የማይጨነቅ ተጫዋችና ግዴለሽ መሳይ ሲሆን ጠጋ ብሎ ለተረዳው ግን ከዚህ ፍጹም የተለየ ሰብእና የነበረው ሰው ነበር። ተሻለ በጣም ተፃራሪ በሆኑ ሁለት ሁኔታዎች ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ ፅናት (Consistency and integrity) የነበረው የክቡር ህሊና ባለቤት ነበር። እስር ላይ ሆኖ የወላጅ አባቱ ሃብታም ጓደኞች እሱን ከእስር ለማስፈታት የከፍተኛውን ባለስልጣኖች በወቅቱ ተለምዶ እንደነበረው በከፍተኛ ጉቦ አግባብተው የባለሥልጣናቱን ይሁንታ ካረጋገጡ በኋላ አስጠርተው ሊፈታ እንደሚችል ሁኔታውን ሲገልፁለት እድሉን ተጠቅሞ ራሱን በዚህ መንገድ ከማዳን ይልቅ ሌሎች የሚደርስባቸውን ለመቀበል እንደሚመርጥ ዳግመኛም ይህን ጥያቄ እንዳያነሱበት በማስጠንቀቅ ያለመስማማቱን ገልፆ መልሷቸዋል። እንደኔ ይህን እድል የማያገኙ የድሃ ቤተሰብ ልጆችስ ምን ይሁኑ በሚል ያልጠበቁትና መልስ የሌለው ጥያቄ ነበር ሀሳባቸውን እንደማይቀበለው የገለፀላቸው። ተሻለ ይህን ሲወስን ህይወት ጠርዝ ላይ ቆሞ ሞት አፍጦ እየጠበቀው ከሚቀጥሉት ቀናት ባንዱ ከሚገደሉት የድርጅቱ አባላት ዋነኛው እንደሆነ በሚገባ እያወቀው እንጂ እድን ይሆናል የሚል ቅንጣትም ተስፋ ይዞ አልነበረም። ከዚህ በተጨማሪ እስረኛው የሜይ ዴይን በዓል እንዲያከብር ታዞ በዚህም ምክንያት ጥበቃው ላላ ብሎ ስለነበረ ተሻለን ለምን ሾልከኽ ባጥር ዘለህ አታመልጥም የሚል ጥያቄ ባቀርብለት በኔ የተነሳ ሌላው እስረኛ ጉዳት እንዲደርስበት አልፈልግም ብሎ ሀሳቡን

ሳይቀበለው ቀርቷል። በርግጥም ተሻለ ይህን ተግባራዊ ቢያደርገው ኖሮ መዘዙ ለሌሎች ይተርፍ እንደነበር ከዛ በኋላ በተፈጠሩት አጋጣሚዎች ተረጋግጧል። ተሻለ እንዲህ ያለ የከበረ ህሊና ባለቤት ነበር ራሱን ላመነበትና ለሌሎች አሳልፎ የሰጠ ታላቅ ሰው።

ሌላው በዚህ አጭር ማስታወሻ ከሚወሱት አንዱ ፅጋዬ ወልዴ (ቻይና) የድርጅት ስሙ ዘምህረት የከፍተኛ 6 ቀበሌ 13 ነዋሪና የቀድሞው ልዑል መኮንን ያሁኑ አዲስ ከተማ አጠቃላይ ት/ቤት ተማሪ የነበረ ሲሆን በተያዘበት ወቅት ምናልባት የሊጉ ወረዳ/ሪጅን/ አባል እንደሆነ ይገመታል። ፅጋዬ ተይዞ ከመታሰሩ በፊት ረዘም ላለ ጊዜ ተሳዳጅ/Fugitive/ ነበረ። እንደተቀሩት ጓዶቹ ሁሉ የያንዳንዷን ቀን ማደሪያውን መፈለግ የሚጀምረው በስሩ የሚገኙትን ሌሎች የሱ ብጤ ተሳዳጅ ጓዶቹ ማደሪያ ማግኘታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ሲሆን አብዛኛውን ሌሊት የሚያሳልፈው ቱቦ ውስጥ፣ መርካቶ ከሚገኙት የጉልት ገበያ መደቦች መሀልና መቃብር ቤቶች ውስጥ ነበር። ወደ መጨረሻም እነዚህ ሁሉ 'ማደሪያዎች' ቅንጦት ሆነው ነበር። ፅጋዬ ከመገደሉ በፊት ዘግናኝ የሆነ ሰቆቃ ቢፈፀምበትም ድርጅቱን አላወገዘም፣ ከሁሉም በላይ የትግል ጓዶቹን ስም አሳልፎ ባለመስጠቱ ዛሬ ከሽብሩ ተርፈው በህይወት ለሚኖሩ ብዙዎች ባለውለታ ነው ሞታቸውን ሞቷልና። ከዕለታት ባንዱ የስቃይ ምሽት ገራፊዎቹ  ፅጋዬን በተከታታይ ድብደባ ቆሞ መሄድ ቀርቶ መቀመጥ እንኳ የተሳነውን ሰውነቱን ደጋግፈው መኪና ላይ በመጫን ወደመኖሪያ ቀበሌው ጽ/ቤት ወረዳ 06/13 በመውሰድ በድርጅቱ አባልነት የሚያውቃቸውን ወጣቶች እንዲጠቁማቸው ያስገድዱታል። ፅጋዬ የሆነ ዘዴ ፈልጎ ጓዶቹን ማዳን ነበረበት። ወዲያውኑ አንድ ሀሳብ መጣለት። የቀበሌው አባላት ያውቁታል የተወሰኑትም በድርጅቱ/ኢህአፓ የተመለመሉ ናቸው ስለሆነም ዜናው በዛው ቅፅበት ለጓዶቹ እንደሚደርስ በማመን የከፍተኛውን ባለሥልጣኖች "ብዙዎቹ መሳሪያ ያላቸው ስለሆነ ከዛሬ ይልቅ ነገ በሚገባ ተጠናክረን ሌሎች የከፍተኛውን አባሎች ጨምረን ብንመጣ ይሻላል" የሚል ሀሳብ ያቀርብላቸዋል አሳሪዎቹም በሃሳቡ ተስማምተው "ፅጋዬ ተባብሮናል" ብለው በመደሰት ወደ እስር ቤቱ ተመለሱ።  በዕቅዱም መሰረት በማግስቱ ከፍተኛ ሀይል አሰባስበው ወደተጠቀሰው ቀበሌ ይሄዳሉ ይሁን እንጂ ፅጋዬ እንደገመተው የአሰሳው ዜና ለቀበሌው ወጣቶች ደርሶ ኖሮ አንድም ወጣት ሳይያዝ ለጊዜውም ቢሆን ከፍጅቱ ማምለጥ ችለዋል።ለፅጋዬ ግን ያ ምሽት ሌላ የጣር ምሽት ነበር ፅጋዬ እንዳታለላቸው ዘግይተው የተረዱት የከፍተኛው ባለሥልጣኖች ፅጋዬን ማሰቃየት የጀመሩት ገና ወደእስር ቤቱ በመመለስ ላይ እያሉ ነበር።

ፅጋዬ ልክ የዛሬ 32 ዓመት በጥቅምት/ኅዳር 70 አ/ም ከአዛለች፣ታጀበና ሌሎችም  ጓዶቹ ጋር ሊገደል ሲወጣ ዛሬ በህይወት ያለ ሌላ የሊጉ አባል እዛው እስር ቤት ውስጥ ተይዞ ስቃይ እየተቀበለ ነበር። ይህ ጓድ በድርጅቱ መዋቅር የፅጋዬ ኮሚቴ አገናኝ ሲሆን የታሰረው ከፅጋዬ ዘግየት ብሎ ነበር። ፅጋዬ እሱን አሳልፎ ቢሰጠው በህይወት የመኖር ዕድሉ ከፍተኛ ነበር እሱ ግን ይህን አላደረገም እንደብዙዎቹ ከሱ በፊትም ሆነ በኋላ እንደሆነው ሁሉ በፅናትና ታማኝነት ምሥጢሩን ጠብቆ የጓዱን ሞት በክብር በመጋፈጥ 'መልካም ዕድል" በማለት ነበር ተሰናብቶት ወደሞት የተጓዘው። ፅጋዬና ተሻለ እንደነ ተስፋዬ ደበሳይ፣ ዮሴፍ አዳነ፣ ግርማቸው ለማ፣ አክሊሉ ሀሩይና ሌሎችም መሪዎቹ ከተራ አባላቱ በፊት ሰማዕትነትን በታላቅ ፅናትና ጀግንነት በተግባር ያሳዩበት ድርጅት ኢሕ አፓ ውስጥ ማደጋቸው ለዚህ ታላቅ ታሪክ ባለቤትነት አብቅቷቸዋል።  ከላይ የተዘረዘረው የተሻለና የፅጋዬ ታሪክ የተናጥል አጋጣሚ ሳይሆን ያብዛኛው የወቅቱ የኢህፓ አባላት ልምድና ታሪክ ነው።

ተሻለ፣ፅጋዬና ሌሎቹም የኢሕአፓ አባላት የተሰዉት አንዳንዶች እንደሚቀባጥሩት ሞት ናፍቋቸውና ለህይወት ግድ አጥተው ሳይሆን ትግሉ መስዋእትነትን ግድ ይል ስለነበረ ብቻ ነው። እውነተኛ ትግል ደግሞ መስዋእት አልባ ላለመሆኑ በግንቦት 97 ምርጫ ለወያኔ የተገበረው የነሺብሬና እስከዛሬም የምሥጢር ግድያው ያላበቃው በሺዎች የሚቆጠሩት ሰማዕታት ደም ማረጋገጫ ነው። ለኢሕአፓ አባላት ህይወትን ማፍቀርና አምባ ገነን ሥርአትን ለመቀየር የሚከፈል መስዋእትነትን መድፈር ተፃራሪ እሴቶች (opposing values) አይደሉም ይልቁንም አምባገነን ሥርአቶችን ለማስወገድ የተከፈሉ/የሚከፈሉ መስዋእትነቶች ለህይወት ከፍተኛውን ዋጋ የመስጠት ማረጋገጫቸው ነው።

ትግሉ ዛሬም በህዝብ ደም የሚነግዱትን የወሬ ማንዴላና ጋንዲዎች ሳይሆን ሀቀኛ ታጋዮችን፣ ህይወትን የሚወዱ ነፃነትን ግን አብልጠው የሚሹ ስለዚህም ሞትን የማይፈሩ ተሻለዎችንና ፅጋዬዎችን መጠየቁና መጠበቁ ግድ ነው። ኢትዮጵያም የምትፈልገው እንደነዚህ አይነቶቹን ነው።

ትላንት ይወደስ የነበረው ይህ አይነቱ ፅናትና ህይወትን ያህል ታላቅ ነገር የሚመጥን ክቡር ህሊና ዛሬ በሚያሳዝንና በሚያስደነግጥ ሁኔታ ፈተና ላይ ወድቆ ማየትን ያህል ልብን ሰባሪ ክስተት ይኖራል ማለት ይከብዳል። ዛሬ አርበኝነትና ፅናት ከኋላ ቀርነትና ከሞኝነት ተመድቧል።  መንፈስ ደካሞች ሰብእናቸውንና ህሊናቸውን ለሚያልፍ ጊዜያዊ ጥቅም ለድርድር የሚያቀርቡትን ያህል የፀኑቱ ደግሞ የሀገርና የመጪውን ትውልድ እጣ ፈንታ ከዛሬው ወቅታዊ ችግራቸው ባሻገር ለማየት የበረቱት፣ ቃል የእምነት ዕዳ የሆነባቸው

ቃልኪዳንን ማክበር እንደሚቻል የህይወት ዋጋ ከፍለው አስተምረውናል እያስተማሩንም ነው። (ደብተራውን አበራሽን...ያስታውሷል) ስለዚህም እናከብራቸዋለን ለዘላለሙም ባለውለታዎቻችን ናቸው።